# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 80 ህዳር 17 2002 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ወያኔ “ግብር” ወይም “ታክስ” ብሎ የሚጠራቸው ነገሮች እውነተኛ ስማቸው “ንጥቂያ” ወይም “ዝርፊያ” ነው። ንብረታችንን ከኪስ አውላቂ የመጠበቅ መብት እንዳለን ሁሉ በተቻለን መጠን ከወያኔ ንጥቂያና ዝርፊያ ራሳችንን መጠበቅ ተቀባይነት ያለው ተግባር ነው።

. . . ዝርዝሩን ገጽ 2

## የወያኔው አቃቢ ህግ በገንቦት 7 አባላትና በእነ ጄ/ል ተፈራ ማሞ ላይ የሞት ብይን እንዲሰጥ ሲጠይቅ፣ የተወሰኑት ተከሳሾች የፍርድ ቤት ድራማ በማንቋሸሽ መልስ አንሰጥም ሲሉ ተናገሩ

ችሎቱን ከተከታተሉት ጋዜጠኞች ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው ወያኔ የግንቦት 7 አባላት የሆኑትን ጨምሮ በእስር ላይ በሚገኙት 25 ወታደራዊ መኮንኖች እና ሲቪሎች ላይ የሞት ቅጣት እንዲበየን የይስሙላውን ፍርድ ቤት ጠይቋል። የወያኔው አቃቢ ህግ የሞት ቅጣቱ እንዲወሰን የጠየቀው ቅጣቱ ለሌሎችም ማስጠንቀቂያና ማስተማሪያ እንዲሆን ነው ማለቱ ታውቋል። ወያኔ እንደፈለገ በሚያሽከረክረው ፍርድቤት የሞት ቅጣትና የንብረት መውረስ ውሳኔዎችን በማስወሰን ለነጻነት የሚደረገውን ህዝባዊ ትግል አቆማለሁ ብሎ ማለሙ በዙሪያው የተሰባሰቡት ድውያን አሁንም ከታሪክ ለመማር ያልቻሉ ፍጡሮች መሆናቸውን እንደሚያሳይ ብዙዎች ይስማማሉ። ኢትዮጵያ ለነጻነታቸው ሲሉ ህይወታቸውን የሰው በርካታ ጅግኖች የሞሉባት አገር መሆኑዋ እየታወቀ፣ የባንዳ ውላጅ የሆነው መለስ ዜናዊ ግን ይህን ታሪክ ልብ ሳይል አሁንም ዜጎችን በህይወታቸውና በንብረታቸው በማስፈራራት ለነጻነት የሚያደርጉትን ትግል ለመቀልበስ የሚችል ይመስለዋል። በአዲስ አበባ እምብርት ላይ የቆሙት የሚኒሊክና የአቡነ ጴጥሮስ ሀውልቶች ነጻነትን በጉልበት ማፈን እንችላለን ብለው ለሚያስቡት ድውያን “አትችሉም” የሚል ትምህርት ለመስጠት የቆሙ መሆናቸውን የወያኔው አገዛዝ እስካሁን ልብ እንዳላለው የሰሞኑ የፍርድቤት ድራማ ህያው ምስክር ነው ተብሎአል።

የወያኔው አቃቢ ህግ በሁሉም ተከሳሾች ላይ የሞት ፍርድ እንዲፈረድባቸው በጠየቀ ጊዜ አንዳንድ ተከሳሾች የወያኔን የፍርድቤት ድራማ አፈር ድሜ የሚያስበላ፣ ጄ/ል መንግስቱ ንዋይ በአጼ ሀይለስላሴ ዘመን በተመሳሳይ ወንጀል ተከሰው በነበረበት ጊዜ ካደረጉት ንግግር የሚመሳሰል ጠንካራ ንግግር ተናግረዋል። አራት ተከሳሾች ፣ ሻለቃ ወርቁ አለሙ፣ ብቸኛ የ ሴት የነጻነት አርበኛ የሆኑትን ጀግናዋን ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ፣ ሻለቃ መኮንን ወርቁ ና አንድ ስማቸው ያልተጠቀሰ የነጻነት አርበኛ፣ ከወያኔው ፍርድ ቤት ምንም ደግ ነገር ስለማንጠብቅ የምንሰጠው የፍርድ አስተያየት የለም ሲሉ ተናግረዋል። ሻለቃ ወርቁ “ማረሚያ ቤት ከተፈጸመብኝ ግፍ የከፋ ፍርድ ስለማይመጣ ምንም የፍርድ ማቅለያ የለኝም፣ ፍትህ በሌለበት አገር ምን አይነት ፍትህ እንድጠብቅ ይጠበቃል ሲሉ፣ ሌላው ስማቸውን በትክክል ለመመዝገብ ያልቻነው ጀግና ኢትዮጵያዊ ደግሞ “ ምንም የምናገረው ነገር የለኝም። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የአሜሪካ የእርዳታ ፕሮግራም ከወያኔ ኩባንያ ጋር አብሮ ለመስራት ስመምነት ላይ በመድረሱ ከፍተኛ ትችት ቀረበበት፣ የኦባማ አስተዳደርን የዲሞክራሲ ቁርጠኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚከትም ነው

እንደፈረንጆች አቆጣጠር በ 2000 አም የተቋቋመውና በምህጻረ ቃል አጎዋ እየተባለ የሚጠራው ፕሮጀክት የአፍሪካ ኩባንያዎችን ምርቶች ልዩ በሆነ ታሪፍ ለአሜሪካ ገበያዎች ለማቅረብ ተብሎ በአሜሪካ መንግስት የተዘጋጀተ ፕሮጀክት መሆኑ ሲታወቅ፣ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት በምህጻረ ቃል ዩኤስ.ኤ.አይ.ዲ፣ የህወሀት ኩባንያ የሆነው አልመዳ ጨርቃጨርቅና አትላስ ማንፋክቸሪንግ ግሩፕ የተባለ የአሜሪካ ኩባንያ ስምምነት ላይ እንዲደርሱ የማግባባት ስራ ሰርቷል። አልመዳ የወያኔ ኩባንያ ሆኖ እያለ የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት ኩባንአው ተጠቃሚ እንዲሆን ያደረገው ድለላ ምናልባትም ወያኔ በቅርቡ ዩኤስ አይዲ በፖለቲካ ጣልቃ እየገባ ነው ሲል ላቀረበው ክስ እጅ መንሻ ለማቅረብ ሳይሆን እንዳልቀረ አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ።

የአሜሪካ መንግስት እርሱ የሚደግፋቸው መንግስታት አምባገነኖች ሆኑም አልሆኑም ለዘላለም በስልጣን ላይ እንዲቆዩለት እንደሚፈልግ የሚታወቅ ሲሆን፣ በአለም ተወዳዳሪ የሌላቸውን የነፍሰ ገዳዮች ስብስብ የሀብት ምንጭ የሆነውን የህወሀት ኩባንያ ለመርዳት ያደረገው ሙከራ ይህን አስተያየት እንደሚያጠናክር አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች በመናገር ላይ ናቸው። ኢትዮጵያውያን በኦባማ የቅድመ ምርጫ ንግግር በመተማመን የአሜሪካ መንግስት በወያኔ ላይ ተጽኖ ያሳርፋል ብለው ሲጠብቁ የነበረ ቢሆንም፣ እስካሁን በታየው እውነታ ግን የኦባማ አስተዳደር እንደ ቡሽ አስተዳደር ሁሉ ከአማባገነኖችና ዲሞክራሲን ከሚያፍኑ ሀይሎች ጋር ለመተኛት ወደ ሁዋላ የማይል መሆኑን ነው።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ግንቦት 7 ባለፈው ቅዳሜ በሰሜን አሜሪካይቱ የሀውስተን ከተማ የተሳካ ህዝባዊ ስብሰባ አደረገ

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ በአሜሪካ አገር በሀውስተንና አካባቢዋ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ያደረገው ስብሰባ እጅግ በተሳካ ሁኔታ መካሄዱን የስብሰባው አስተባባሪ ለዝግጅት ክፍላችን ከላከልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል።

የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የአመራር አባላት የሆኑት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋና አቶ ኤፍሬም ማዴቦ እንዲሁም ተጋባዥ እንግዳው አቶ ታማኝ በየነ በተገኙበት በዚህ ስብሰባ ላይ በቅርብ አመታት በከተማይቱ በተደረጉት ተመሳሳይ ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ ታይቶ የማይታወቅ የህዝብ ብዛት የተገኘበት መሆኑንና የኢትዮጵያዊያን ወቅታዊ ሁኔታዎች መነጋገሪያ ፎረም በተባለው ፓልቶክ አማካኝነትም በመላው አለም ተበትነው ለሚገኙ ወገኖቻችንም እንደተላለፈ ተያይዞ የደረሰን ሪፖርት አመለክቷል።

እንደዘጋቢዎቻችን ሪፖርት የተገኘው የተስብሳቢ ብዛት ሁሉንም የዕድሜ ክልል ያካተተና ጉልህ የሆነ የሴቶች ተሳትፎም የታየበት መሆኑ ከመታወቁም በላይ ንቅናቄው ለሚያካሂደው ሁለገብ ትግል ማካሄጃ የሚውል ከፍተኛ የገንዘብ መዋጮ መሰብሰቡን ለማወቅ ተችሎአል። የግንቦት 7 ንቅናቄ በአገር ቤት ሊያካሂደው እየተዘጋጀ ላለው ሁለገብ ትግል ድጋፍ ለማሰባሰብ ኢትዮጵያዊያን በሚኖሩበት አካባቢዎች በመንቀሳቀስ ገለጻ እየሰጠ ያለው የንቅናቄው አመራር፤ አገራችን ስላለችበት ተጨባጭ ሁኔታ ፣ ለነጻነት የሚደረገው ትግል እየገጠሙት ስላለው ውስብስብ ችግሮች እና የመፍተሄ ሃሳቦች ላይ ሰፊ ገለጻና ማብራሪያ የሰጠ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለወያኔ የማደናገሪያ ምርጫ ሰለባ በመሆን ህዝባችን ለመብቱ የሚያደርገውን መራራ ትግል የሚያግዝ እርምጃ ሳይሆን ተቃራኒውን አቋም በመያዝ ለወያኔ እድሜ ማራዘሚያ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ስለተነሱ ተቃዋሚ ነን ሰለሚሉ አንዳንድ ድርጅቶች ከተሰብሳቢው ጥያቄ ቀርቦ አጥጋቢ ምላሽ ተሰጥቶበታል። አገራችንን ለከፋ ጉስቁልና እና ድህነት ብቻ ሳይሆን ዜጎቿንም ታይቶ በማይታወቅ ዘረኛ አገዛዝ ረግጦ እየገዛ ያለውን የዘረኞች ጥርቅም ከህዝባችን ጫንቃ አሽቀንጥሮ ለመጣል በውጭ አገር ከሚገኘው ኢትዮጵያዊ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የአገራችንን መሬት ለውጭ አገራት ኩባንያዎች ለመሸጥ የሚአደርገውን እሩጫ ኢትዮጵያውአን አምርረው ሊታገሉት እንደሚገባ ተገለጸ

ዘጋቢያችን ሰሞኑን የሳኡዲና የሌሎች አገሮች ባለሀብቶች የኢትዮጵያን መሬት ለመቀራመት በብዛት ወደ ኢትዮጵያ መጉረፋቸውን በማስመልከት ላቀረበው ጥያቄ፣ ነዋሪዎች በሰጡት አስተያየት ድርጊቱን በአስኳይ መቃወም እንደሚገባ ገልጸዋል።

ሼክ ረዲማን የተባሉ የመርካቶ ነዋሪ ሲናገሩ “ድሮ መሪዎቻችን መሬታችንን አንሰጥም ብለው ተዋግተው አልፈዋል። የአሁኖቹ ደግሞ መሬታችንን ውሰዱ እያሉ ይለምናሉ። እንዲህ ያለው አገርን የመሸጥ ነገር ለእኔ አይገባኝም። ይህን አምርሬ እቃወማለሁ “ብለዋል። አሁንም በመርካቶ አካባቢ በአስመጪና ላኪነት የሚሰሩ አንድ ግለሰብ እንደተናገሩት “ቻይናና ህንድ ህዝብ በዝቶባቸው የሚያርሱት መሬት ሲያጡ የእኛን ለመቀራመት አሰፍስፈው በመጠባበቅ ላይ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ምርቱን አምርተው ወደ አገራቸው ነው የሚልኩት። እዚህ አገር እንዳይሸጡ ሰው የመግዛት አቅም የለውም። መሸጥ የሚፈልጉትም በዶላር ወይም በዩሮ ነው። የእኛ ሰው ደግሞ እንኳን ዶላሩ ምኑም የለውም። ስለዚህ ኩባንያዎቹ መሸጥ የሚፈልጉት ለአገራቸው ነው። እዚሁ ሽጡ ብለን ልናስገድዳቸው አንችልም።” ሲሉ ተናገረዋል። አቶ እወነቱ ፈለቀ ሲናገሩ ደግሞ “እኛው ራሳችን ኑና ቅኝ ግዙን እያልናቸው ነው። መለስ ዜናዊ የአባቱንና የአያቱን የባንዳነት ታሪክ እየደገመ ነው። አገራችንን ለቅኝ ግዛት አሳልፎ እያሰጣት ነው። እርሱ ለኢትዮጵያ ህዝብ አስቦ ሳይሆን የውጭ ምንዛሬ ስላጠረው ያንን ለማሙዋለት ነው መሬት የሚቸበችበው። የቸበቸበውንም ገንዘብ ይዞ ይጠፋል። ኢትዮጵያውያን በተለይም በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ና በቤንሻንጉል ጉሙዝ አካባቢዎች ያሉ ኢትዮጵያውያን ብዙው መሬት በእነዚህ አካባቢዎች የሚወሰድ በመሆኑ አጥብቀው መቃወም አለባቸው” ሲሉ ምክራቸውን ለግሰዋል።

አቶ ማሞ በሻህ ሲናገሩ ድግሞ በርካታ ገበሬዎች እየተፈናቀሉ ነው፣ እነዚህ ገበሬዎች እኮ ዜጎች ናቸው ። ይልቅ ቻይና እዳደረገው ገበሬዎች በደንብ እንዲያመርቱ ማበረታታትና እራሳችንን እንድንችል ማድረግ ሲገባ መሬት መቸርቸር ተገቢ አይደለም” ካሉ በሁዋላ፣ ወያኔ በምግብ ራሳችንን ችለናል እያለ ሲያናፍሰው የነበረው ወሬ ሁሉ የት ገብቶ ነው ዛሬ ለውጭ ኩባንያዎች መሬት ካልሸጥን ከረሀብ አንወጣም የሚባለው ሲሉ ጠይቀዋል።” (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በግብር ስም እየተደረገ ያለውን ዘረፋ ማስቆም የሁላችንም ኃላፊነት ነው!!!

*ተዘዋዋሪ ወንበዴዎች ነጥቀው ይሮጣሉ፤ ተመልሰውም ይደግማሉ። እነዚህ ወንበዴዎች ነጥቀው በሮጡ ቁጥር የማኅበረሰቡ ሃብት የማፍራት ፍላጎት ስለሚዳከም በሚቀጥለው ዙር የሚዘርፉት ነገር እያነሰባቸው ይመጣል። ቀን ባለፈ መጠን ነጥቆ መሮጥ ዞሮ ዞሮ እነሱኑ እንደሚጎዳቸው ይገነዘቡና ራሳቸውን ከተዘዋዋሪ ወንበዴነት ወደ ሰፋሪ ወንበዴነት ይቀይራሉ። ተደላድለው በመቀመጥም ይዞታቸውን ከሌሎች ወንበዴዎች በመከላከል ሰላምን አሰፈንንልህ ይሉታል። ከዚያም ለንጥቂያቸው ሥርዓትና ልክ ያበጁለታል፤ ስሙንም "ግብር" ይሉታል[1]።*

እውቁ ኢኮኖሚስት ማንኩር ኦልሰን ያሉትን ነው ከላይ የጠቀስነው። የግጥምጥሙ መብዛት እኚህ ምሁር ወያኔን እያሰቡ ነበር እንዴ የፃፉት? ያሰኛል። እሳቸው ግን በአጠቃላይ አምባገነኖችን እያሰቡ ነው የፃፉት።

ወያኔ ከደደቢት በረሃ ወደ ምኒሊክ ቤተመንግሥት ያደረገው ጉዞ ነጥቆ ከመሮጥ ወደ ቁጭ ብሎ መምጠጥ እየተደረገ ያለ ሽግግር ነው። ወያኔ አሁን እንደበፊቱ የባንክ ካዝና መስበር አያስፈልገውም፤ የባንክ ኃላፊው ገንዘቡን ይዞ እንዲመጣ ማድረግ ይቻለዋልና። የአንዱን ጥሮ አዳሪ ቤት ወሮ ሃብቱን በማጋዝ ከመቸገር "ይህን ያህል ግብር ስላለብህ መጥተህ ክፈል" ማለት ይቀላል። ያም ሆኖ ግን ገና በሽግግር ላይ ነው። ወያኔ በሃያ ዓመታት ከነጥቆ ሩጫ ወደ ቁጭ ብሎ መምጠጥ እንኳን ሙሉ በሙሉ መሸጋገር አልቻለም። ይህ ሽግግር ዛሬ ድረስ ላለመጠናቀቁ ጉልህ ማረጋገጫው ለንጥቂያው **ሥርዓት** እና **ልክ** ማበጀት አለመቻሉ ነው። ኦልሰን ያነሷቸው ሌሎች ወንበዴዎች ንጥቂያቸው "ግብር" እንዲሰኝ ያስቻሏቸው ሥርዓትና ልክ የሚከተሉት ዘጠኝ ታዋቂ የግብር መርሆች ናቸው።

1. **እኩልነት** – በተለያዩ የሥራ መስኮች ቢሰማሩም እንኳን ሁለት ተመሳሳይ ገቢ ያላቸው ሰዎች ተመሳሳይ መጠን ያለው ግብር መክፈል አለባቸው፤
2. **እርግጠኝነት** – የግብር መጠን በአስከፋዩ በዘፈቀደ የሚወሰን ሳይሆን ከፋዩም አስልቶ ሊደርስበት የሚችል መሆን ይኖርበታል፤
3. **አመቺነት** – የግብር መክፈያ ጊዜና አከፋፈሉ ለግብር ሰብሳቢው ሳይሆን ለከፋዩ አመቺ መሆን ይኖርበታል፤
4. **ወጪ ቆጣቢነት** – የግብር አሰባሰቡ ዘዴ ወጪ ቆጣቢ መሆን ይኖርበታል፤ በተለይም የግብር ከፋዮችን ጊዜና ጉልበት ማባከን የለበትም፤
5. **ምርታማነት** – ከግብር የሚሰበሰበው ገንዘብ የመንግሥትን ወጪዎች ለመሸፈን የሚበቃ ያህል መሆን ይኖርበታል፤
6. **ተንሳፋፊነት/ብሩህነት** – ኢኮኖሚው ሲያድግ የግብር ምጣኔውም ሆነ የግብር ዓይነቶች ላይ ለውጥ ባይደረግም እንኳን የግብር ገቢው መጠን ማደግ ይኖርበታል፤
7. **ተለማጭነት** – የግብር ሥርዓቱ በኢኮኖሚው አዎንታዊ ለውጦችን ለማምጣት እንዲያስችሉ አድርጎ ለመቀየር የሚያመች መሆን ይኖርበታል፤
8. **ቀላልነት** – የግብር ሥርዓቱ ቀላልና የሂሳብ ሙያ የሌለውም ሰው በቀላሉ ሊረዳው የሚችል መሆን ይኖርበታል፤ እና
9. **ሁሉን ዓቀፍነት** – በአንድ ወይም በሁለት የግብር ዓይነቶች ከመወሰን በርካታ የግብር ዓይነቶችን ሥራ ላይ በማዋል ሁሉንም ዓይነት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በመዳሰስ የግብር ጫና በጥቂቶች ትከሻ ላይ እንዳይወድቅ ማድረግ ያስፈልጋል።

የወያኔ ንጥቂያ ከላይ ከተዘረዘሩት መርሆች ውስጥ **አንዱንም** አያሟላም። ለምሳሌ የእኩልነት መርህን ብንመረምር እንኳንስ እንደሌላው ሁሉ እኩል ግብር ሊከፍሉ ቀርቶ ድጎማ የሚደረግላቸው ኤፈርትና መሰል ቅምጥሎች አሉ። የወያኔ የንጥቂያ ሥርዓት በአድልዎ የተሞላ፤ ተቀናቃኝን ለማዳከም በሥራ ላይ የሚውል የዘረኛ ፖለቲካ ማራመጃ መሣሪያ ነው።

የእርግጠኝነት መርህም በወያኔ ዘረፋ ቦታ የለውም። ማጅራት መቺ "ያለህን ዘርግፍ" እንደሚል ሁሉ የወያኔ ሎሌዎች በጭንቅላታቸው የመጣላቸውን ትልቅ ቁጥር በሚጠሉት ነጋዴ ላይ በግብር እዳነት መጫን የተለመደ ነው። በወያኔ ጥርስ ለተነከሰበት የሂሳብ መዝገብ ይዞ መቅረብ እንኳን ከግምት ግብር አያድንም።

አመቺነትን በተመለከተም ጌታው ግብር ሰብሳቢው እንጂ ከፋዩ ሆኖ አያውቅም። እንዲህ እያልን ዘጠኙንም መርሆች በየተራ ብንመረምር የወያኔ "ግብር" ገና ያልሰከነ ወንበዴ የሚያደረገው ዘረፋ መሆኑን በስሜት ሳይሆን በበቂ ምክንያቶች አስረግጠን ማስረዳት እንችላለን።

ወያኔ በምርጫ 97 ሰሞን ግብርን በድምጽ መግዣነት መጠቀሙ የምናስታውሰው ነው። ዛሬ ተቃዋሚዎች የተዳከሙ፤ እሱ ደግሞ የጠነከረ ሲመስለው የያኔው ቅናሽ ከማስመለስም በላይ መቸም ቢሆን በማይረካ ስግብግብነት ዘረፋው ጣራ እንዲነካ አድርጎ ቀድሞውኑ የደከመውን ኢኮኖሚ ጭራሹን እየገደለው ነው። በዚህ ዘረፋ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ሠርቶ የእለት ጉርስን መቻል ታላቅ ስኬት እየሆነ ነው። በተለይም የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የጉምሩክ ቀረጥ ተቀናቃኞችን ነጥሎ ለመምታት የተጠመዱ ድምፅ–አልባ መሣሪያዎች ናቸው።

ወያኔ ዘረፋውን "ግብር" ብሎ መጥራቱ ሳያንሰው ወደንና ፈቅደን ልንከፍለው የሚገባ "የዜግነት ግዴታ" እንደሆነ ይሰብከናል። ለመሆኑ ወደንና ፈቅደን እንድንዘረፍ እንደምን ይጠበቅብናል? ዘረፋን ሳይሆን ግብርን እንኳን ወደንና ፈቅደን ለመክፈል "በሰበሰብከው ገንዘብ ምን ሰራህበት?" ብለን የምንጠይቀው መንግሥት ሊኖረን ይገባል። ለማይወክለን ወይም መልካም ነገሮችን ለማያቀርብልን መንግሥት አንገብርም ማለት ድሮም የነበረ ነገር ነው። አሁን እኛ የገባንበት ሁኔታ ግን ከዚህ እጅግ የባሰ ነው። ጉዳያችን ያለው ከመንግሥት ጋር ሳይሆን ገና ካልሰከኑ ወንበዴዎች ጋር ነው።

ወያኔ "ግብር" ወይም "ታክስ" ብሎ የሚጠራቸው ነገሮች እውነተኛ ስማቸው "ንጥቂያ" ወይም "ዝርፊያ" ነው። ንብረታችንን ከኪስ አውላቂ የመጠበቅ መብት እንዳለን ሁሉ በተቻለን መጠን ከወያኔ ንጥቂያና ዝርፊያ ራሳችንን መጠበቅ ተቀባይነት ያለው ተግባር ነው። እንዲያውም ለወያኔ ግብር አለመክፈል የሕዝብ ሃብት በወንበዴዎች እጅ እንዳይወቅድ የሚያደርግ የሚወደስ አኩሪ ተግባር ነው።

ስለሆነም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በተናጠልም ሆነ በቡድን ባመቸው መንገድ ሁሉ ተጠቅሞ ወያኔ በግብርና ታክስ ስም የሚያደርገውን ዝርፊያ እንዲያመክን ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ጥሪ ያደርጋል። በግብር ስም እየተደረገ ያለውን ዘረፋ ማስቆም የሁላችንም ኃላፊነት ነው!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

[1] *Olson Mancure "Dictatorship, Democracy and Development" American Political Science Review Vol. 87 No. 3 PP. 567-576*

### የአሜሪካ የእርዳታ ፕሮግራም ከወያኔ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በአሜሪካ ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የኦባማ አስተዳደር ከአምባገነኑና ነፍሰ ገዳዩ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋር የሚያደርገውን መሞዳሞድ እንዲያቆም ግፊት ማድረግ እንደሚገባቸው በአሜሪካ የሚኖሩ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ገልጸዋል። ኢትዮጵያውአኑ ለግንቦት 7 ድምጽ በሰጡት አስተያየት "የአሜሪካ መንግስት በታክስ ስም የሚሰበስበውን ገንዘብ ነጻነታችንን ለሚገፉት ሀይሎች አሳልፎ በመስጠት፣ ነጻነታችንን እንድንነጠቅ እያደረገን በመሆኑ ልንቃወመው ይገባናል ብላል።

ብሉም በርግ የተባለው ታዋቂ ድህረ ገጽ ባቀረበው ዘገባ የአለም ባንክ የህወሀት ኩባንያዎች የሀብት ምንጭና የገንዘብ ዝውውር እንዲሁም የሂሳብ ሪፖርት አለመታወቁ በእጅጉ እንዳሳሰበው ጠቅሷል።

### ግንቦት 7 ባለፈው ቅዳሜ በሰሜን አሜሪካይቱ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ዜጋ ምን እንደሚጠበቅ በግልጽ በተወያየው በዚህ ስብሰባ እጅግ የተመሰጡ ወጣቶች አስፈላጊውን የትግል ድርሻ ለማበርከት "ምን ማድረግ እንዳለብን አሁኑኑ ንገሩን" በማለት ወኔ በተሞላበት የአገር ፍቅር ስሜት በመድረክ ላይ የነበሩትን የአመራር አባላት ሲጠይቁ ተስተውለዋል።

በመጨረሻም ለንቅናቄው አመራር አባላት በተዘጋጀው የእራት ግብዣ ሥነሥርዓት ላይ በርካታ ስዎች የተገኙ መሆናቸውና በዚሁ ዕለት ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ ነጻነት ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ትግሉን በመቀላቀል የግንቦት 7ን ድርጅታዊ መዋቅር በከተማው ውስጥ መዘርጋታቸው ታውቆአል ።

ግንቦት 7 በሰሜን አሜሪካ የሚያካሂደውን ህዝባዊ ስብሰባ በመቀጠል እንደፈረንጆች አቆጣጠር በመጪው ወር ዲሰምበር 5 በኮሎምቦስ ኦሃዮና አካባቢዎቹ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጋር ተመሳሳይ ስብሰባ እንደሚያደርግ ከንቅናቄው ህዝብ ግንኙነት ያገኘነው መረጃ አረጋግጦአል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## አንበሳን አምበረክካለሁ ብሎ ማሰብ እብደት ሲሆን አንበሳን አምበርክኪያለሁ ብሎ ማመን ደግሞ አንበሳ የሚያድነዉና በክርንም የሚያቀምሰው ተንበርክኮ እንደሆነ ካለማወቅ የሚመነጭ ደካማ አስተሳሰብ ነው

ከታገል ለነጻነት

ያለፉት ሃያ የግፍ ዓመታት የወያኔ ኢሃዴግ ዋነኛ አጀንዳና ተግባር የተናጠል ወይም የጅምላ አሰቃቂ ርምጃዎችን በመውሰድ የኢትዮጵያን ህዝብ አንገት ማስደፋት፤ ቅስም መስበርና ማምበርከክ ብሎም በዘር ላይ የተመሰረተ አምባገነንነትን የመትከል ቅዠት እንደሆነ ለማንም የተደበቀ ሚስጥር አይደለም። ቀደም ብሉ በጀግናዋ ብርቱካን ሚዴቅሳና መሰል ዉድ ኢትዮጵያዊያን፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በነ ጀነራል ተፈራ ማሞ፡ አሳምነው ጽጌና ሌሎችም ውድ ጀግና ኢትዮጵያዊያን ላይ ወያኔ ኢአዴግ እየወሰዳቸው ያሉ በቃላት ለመግለጽ የሚያስቸግሩ ሰቆቃዎች፡ እንዲሁም ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ በተደጋጋሚ በርካታ ኢትዮጵያዊያንን ደመከልብ ያደረጉ ግድያዎች፡ በብዙ ሽህ በሚቆጠሩት ላይ ደግሞ እየተፈጸሙ ያሉት የእስራትና የማዋከብ ተግባራት ወያኔ ኢሃዴግ በተናጠልና በጅምላ እያደረሳቸው ካሉት በርካታ የቅስም ሰበራ ሙከራዎች ሊጠቀሱ የሚችሉ ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው። የሃይማኖትና ሌሎች ባህላዊና የተከበሩ ማህበራዊ ተቋማትን የማዋረድና የማንኮታኮት፡ ኢትዮጵያዊያንን በዘርና በሃይማኖት በመከፋፈል እርስ በርስ እንዲናቆሩ የማድረግ ፡ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያለምንም ፍላጎቱ በማስገደድ በጅምላ የወያኔ አባል የማድረግ ሙከራና ሆድ አደሮችን የጥቅማጥቅም ፍርፋሪዉና የርካሽ ተግባሩ ተካፋይ የማድረግ እረፍት የለሽ የሌት ከቀን ተግባሩ ሁሉ ድምር አላማ ህዝብን በጉልበቱ በማፈን ተስፋ የማስቆረጥና ቅስም የመስበር ለመሆኑ ቅንጣት ታክል የሚያጠራጥረን አይደለም።

ወያኔ ኢሃዴግ ባስቀመጠው አሻንጉሊትና ወራዳ ፍርድ ቤት ተባባሪነት ቀደም ብሎ በራሱ መንግስት ተብየ ባለስልጣናትና የጦር አዛዦች ዘንድ ሳይቀር በጀግንነታቸው የሚታወቁትንና በሰራዊቱ ዉስጥም ተወዳጅ የሆኑትን፣ ጄኔራል ተፈራ ማሞንና አሳምነው ጽጌን ጨምሮ በሌሎችም ዉድ ኢትዮጵያዊያን ላይ፣ አይንን ያህል አካል እስኪጎድል የሚያደርስ ድብደባ፡ ብልት ቅጥቀጣ እና በኤሌክትሪክ ኃይል በሚሞቅ መሳሪያ ጭንቅላትን የማጋል ሰቆቃዎች በአደባባይ ተፈጽመውባቸዋል። ወያኔ በ መዳፉ ውስጥ ያሉትን የፓለቲካ እስረኞች እንደ አስጊነታቸውና ታዋቂነታቸው መጠን እንዲህ ዓይነት ሰቆቃ የመፈጸሙ ዋናዉ ዓላማ እነኝህ ብርቅና ድንቅ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን የሰቆቃ ህይወት ገፈትን እንዲቀምሱ በማድረግ 'እኔን ያየህ ተቀጣ' እንዲሉና ቀሪዉም የኢትዮጵያ ህዝብ በእነኝህ ጀግኖች ላይ የደረሰዉን ሰቆቃ በማየት በፍርሃት ድባብ ዉስጥ ገብቶ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ ለማድረግ በማሰብ ነው። ይሁን እንጂ ወያኔ እያደረገ ካላቸው ከላይ የተገለጹት አሰቃቂ ተግባራት በተቃራኒ አንገቱን እየደፋና እየተንበረከከ የመሰለው የኢትዮጵያ ህዝብና ዉዶቹ ጀግኖቻችን ለወያኔ የግፍ አገዛዝ አለመንበርከካቸውን የልቁንም አመቺ ሁኔታን በመናፈቅና አድፍጠው በመጠባበቅ ላይ ያሉ መሆኑን በተለያየ መልኩ በመግለጽና በማረጋገጥ ላይ የሚገኙ ሲሆን በእብሪት ያበጠዉና የደነዘዘው ወያኔ ኢሃዴግ ግን ይህን የተዳፈነ የእሳት ረመጥ ልብ ያለውና የተረዳው አይመስልም።

በቅርብ ቀን የወያኔው ኢህአዴግ ቁኘጮ መለስ ዜናዊ የአዲስ አበባን ወጣቶች የራሱን ምስል ያስለለጠፈበትን ካናቴራ አልብሶ ለሶስተኛ ጊዜ በሚለኒየም አዳራሽ በመሰብሰብ የተለመደዉን ስብከትና የፖለቲካ ጠመቃ ተግባሩን በማከናወን ወጣቶቹን በእጄ ዉስጥ አስገብቻለሁ ብሎም አምበርክኪያለሁ ብሎ ባመነበት ዕለት ማግስት በተካሄደዉ ዓመታዊ የአዲስ አበባው ታላቁ ሩጫ አስደንጋጭ በሆነ መልኩ የአዲስ አበባ ወጣቶች ያላቸዉን ዉስጣዊ ቁጭት፡ አቋዋምና ግልጽ መለእክት በማያወላውል መልኩ ልቡ ላበጠበት ወያኔ ባደባባይ አስተላልፈዋል። ከሰላሳ ሶስት ሺህ ህዝብ በላይ እንደተሳተፈበት በተዘገበው ታላቁ ሩጫ በአዲስ አበባ ወጣቶች አንበሳዋ ብርቱካን ሚዴቅሳ ከእስር እንደትፈታ የሚያስጠነቅቅ ጩኸት ከመስተጋባቱም በላይ " እንነጋገር እንነጋገር የቡርቴን ነገር..." ፤ "... ይረሳል እንዴት ይረሳል የቡርቴ ነገር...."፤ "ቡርቱካን ማንዴላ ልደቱ ሌባ"፤ "ቡርቱየ ጀግና ልደቱ ሌባ"፤ "ልደቱ ይሰቀል"፤ "ወኔ የሌለው ሃይሉ ሻውል ነው"፤ "ኃይሉ ሻውል ወኔ የለዉም፣ ኃይሉ ሽሉ"፤ "ልደቱ አቤት ውሽቱ'፤' "ጫሚሶ ሌባ"፤ "ስድስት ወር ብቻ ስድስት ወር ብቻ መሰናበቻ--- እንደፈራችሁ ደረስንባችሁ"፤ "ፍትህ የሌለው ፍትህ ሚኒስቴር ነው" "ደም ደም ይሸታል ቤቱ ቤተ መንግሥቱ፤ ወዘተ በሚሉ መፈክሮች አንበሶቹ ወጣቶች በወያኔ ኢሃዴግ ቤተመንግስትና ተቋዋማት ላይ በአንድነት አግስተዋል። ወጣቶቹ በዚህ ብቻም አላቆሙም ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች የሚቃወማቸዉ በዉጭ አገር የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ እንጂ በአገር ቤት ያለው እንደሚደግፉቸዉና ከየቦታዉም ድጋፍ እያደረገላቸው እንደሆነ ቢናገሩም በታላቁ የብሶት መግለጫ ሩጫ ላይ ወጣቶቹ ወዳጅና ጠላትን ለይተዉ የሚያውቁ ብቻ ሳይሆን በድህረ ምርጫ 97 በመለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ በአጋዚ ጦር የተጨፈጨፉት በርካታ ወገኖቻቸው የተሰውለት የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ ከግምት ሳይገባ ወያኔ እድሜውን ለማራዘም ባዘጋጀው ድርድር ተብዬ ተውነት ውስጥ ተገብቶ ሊመጣ የሚችል መሰረታዊ ለውጥ እንደማይኖር እምነታቸውን በአደባባይ ገልጸዋል። አጋጣሚው ቢመቻችላቸው ነጻነታቸውን ለመቀዳጀት ለሚደረገው ትግል ከማን ጋር እንደሚወግኑም ፍንጭ ሰጥተዋል።

ነጻነት ከምንም በላይ እንደሆነ የተረዱት እነኚህ ወጣቶች ያለባቸዉን የድህነት ህይወትና ኑሮ እንኳን ቦታ ሳይሰጡ አንዲት ቲሸርት በሃምሳ ብር በመግዛትና በሩጫዉም በመሳተፍ "ሃምሳ ብራችን ነጻነታችን" ሲሉ መደመጣቸው ለኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነት ከምንም ነገር በላይ የሆነ የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ መሆኑን ያረጋገጠ እዉነት ሆኖ አልፏል። ልብ ላለዉና ልብ ላለ የኢትዮጵያ ህዝብ፡ ወያኔ ኢህአዴግንና አሽቃባጮቹን « ወዮዉላችሁ ፤ ይግባችሁ፡ በነጻነታችን ምንም አይነት ድርድር አይኖርም፡ ይህንም የማትረዱ ከሆናችሁ ከስድስት ወር በኋላ እናሳያቹሃለን» በማለት ወደፊት ሊደርስ ከሚችለዉ አደጋ መጠንቀቅ ይቻል ዘንድ ለልበ ቢሶቹ ግልጽ የሆኑ ማስጠንቀቂያዎቻቸዉን ሰጥተዋል። የነኝህ ወጣቶች ጩኸትና ማስጠንቀቂያ ግፈኛዉ ወያኔ ለሕዝባዊ ጥያቄዎች አስቸኳይ ምላሽ መስጠት ካልቻለና ራሱንም ለብሄራዊ እርቅ ሊያዘጋጅ ካልቻለ የተዳፈነው የሕዝብ ቁጣ እሳት ረመጥ በቀላሉ ሊቀጣጠልና ከፍተኛ ጥፋትንም ሊያስከትል እንደሚችል የሚያረጋግጥ ለመሆኑ በርካቶች ይስማሙበታል።

ለወያኔ ኢህአዴግ ዜጎችን የማምበርከክ የማያቋርጥ ጥረትና ሙከራ በቅድሚያ አንበሳይቱ ብርቱካን ሚዴቅሳ *"በእኔ እምነት ይሄ ሁሉ ከሕግ የወጣ ዛቻና ማስፈራሪያ እየደረሰብን ያለው ስለ ቃላት ጨዋታ ወይም ስለ ተዛባ እውነት ወይም ስለተጣሰ ሕግ አይመስለኝም። መልዕክቱ ግልጽ ነው። ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሠላማዊ ታጋዮች። "በሠላማዊና ሕጋዊ ማዕቀፍ ውስጥ የፖለቲካ ትግል ማድረግ የሚቻለው በሕገ መንግሥቱ በተሰመረው መስመር ሳይሆን፤ ገዢው አካል ወይም ግለሰቦች በፈቀዱት ብቻ ነው" የሚል ነው። ለዚህም ደግሞ "እሺ" ወይንም "አዎ" ማለት ለእኔ እጅግ ከባድ ነው።"* በማለት እቅጩን ነግራ የወያኔን ህገወጥ አገዛዝ ግፍ እየተጋተች ነገር ግን እምቢ ለእናንተ አልምበረከክም በማለት ዕዉነትን በመናገሯ ብቻ በእስር ትማቅቃለች። ከቅርብ ቀን ወዲህ ደግሞ አንበሶቹ እነጀኔራል ተፈራ ማሞ በዚሁ ጋጠ ወጥ አገዛዝ የሚደርስባቸውን ተጽኖና ሰቆቃ ተቋቁመው፣ ሁሉም ታሳሪዎች በጋራ በመቆም አፋቸውን ሊዘጉ ያሰቡ ዳኞችን በመንፈስ ብርታት አሸንፈው የደረሰባቸውን ሰቆቃ ለመላው ዓለም በማስረዳት ለወያኔ አሰቃቂ ተግባር ያልተንበረከኩ መሆናቸዉን የማረጋገጥ ዕድል አግኝተዋል፡፡ ይህም የወያኔን ጭካኔ ባደባባይ ለማጋለጥ የፈጸሙት የጀግንነት ተግባር ህዝቡን በእጅጉ ያስደሰተ ሆኗል።

የወያኔ ኢሕአዴግ አገዛዝ እራሱ ያጸደቀዉን ሕገ መንግስት እንኳን ሳያከብር በየጊዜዉ እየናደ ባለበት ሁኔታ፣ በዜጎች ላይ ሰቆቃዊ የተናጠልና የጂምላ የግፍ ርምጃ እየወሰደ ያለ ቢሆንም፤ ሰላማዊ ሰልፍም ሆነ ማናቸዉም ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች በአገሪቷ እንዳይደረግ በተለያየ መንገድ ዉጥረትን በመፍጠር ቢያግድም፣ ዉዶቹ ጀግኖቻችንና የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ባገኙት ቀዳዳ ሁሉ በመግባት ስሜታቸዉንና ተቃዉሞአቸዉን ከመግለጽ የተቆጠቡበት ጊዜ የለም፤ አይኖርም።

ወያኔ ኢህአዴግ ኢትዮጵያዊን አንበሶችንና መላዉንም የኢትዮጵያ ህዝብ አምበረክካለሁ ብሎ ማሰቡ እብደት ሲሆን ምናልባትም ጀግኖቹን አንበሶችና የኢትዮጵያን ህዝብ አምበርክኪያለሁ ብሎ አምኖ ከሆነ አንበሳ የሚያድነዉና በክርንም የሚያቀምሰው ተንበርክኮ እንደሆነ ልብ ሊለው ይገባል እንላለን።

## የወያኔው አቃቢ ህግ በገንቦት 7 አባላትና . . . ከገጽ 1 የዞረ

ለፍትህና ለኢትዮጵያ ትንሳኤ እግዚአብሄርን አደራ እለዋለሁ" ማለታቸው ሲታወቅ፣ ሌሎች ሁለት ጀግኖችም እንዲሁ "ከዚህ ፍርድ ቤት ምንም ፍትህ አንጠብቅም" ማለታቸውን ለማወቅ ችለናል። መላኩ ተፈራ በበኩላቸው ለኢትዮጵአ ዲሞክራሲና ነጻነት ሲሉ ለረጅም ጊዜ በፖለቲካ ትግል ውሰጥ ማሳለፋቸውን በመግለጽ፣ በየትኛውም ህገ ወጥ በሆነ እንቅስቃሴ ወስጥ አልተሳተፍኩም ብለዋል።

እነዚህ ጀግኖች የወያኔን አገዛዝ ማንነት የሚያጋልጥ ንግግር ቢናገሩም አንድም የመገናና ብዙሀን ይህንን ለመመዝገብና ሪፖርት ለማድረግ አለመድፈራቸው በእጅጉ እንደሚያሳፍር ያነጋገርናቸው ሰዎች ጠቅሰዋል። የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የአማርኛው ፕሮግራም ዶቼቬለና የእንግሊዝኛው ክፍሎች ዘገባዎች በእጅጉ እንደሚያሳዝኑዋቸው የገለጹት አስተያየት ሰጪዎች፣ ጀግኖቹ የኢትዮጳያ ልጆች ለህዝባቸው ጠቃሚ መልእክቶችን ቢያቀርቡም የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ግን እነዚህን ንግግሮች ለማቅረብ ወኔ ማጣቱን ገልጸዋል። የጀርመን ራዲዮ ጭራሹን የፍርድ ቤቱን ሂደት ለመዘገብ ወኔ እያጣ መምጣቱን የተናገሩት አስተያየት ሰጪዎች፣ እንኳን ብዙ ህዝብ ሂዶ ሊታዘብ እድል የሌለውን የፍርድ ቤት ውሎ ቀርቶ በታላቁ ሩጫ በአዲስ አበባ ታላላቅ መንገዶች ሲስተጋቡ የዋሉትን ጻረ ወያኔ መፈክሮች እንኳ ለመዘገብ → አለመቻላቸው ወያኔ ለውጭ መገናኛ የሚሰሩትን ሳይቀር ምን ያህል በፍርሃት ድባብ ውስጥ እንደከተታቸው የሚያመላክት ነው ብለዋል።

ወያኔ ህዝቦችን ለማፈን የዘረጋው ሰንሰለት እየተበጣጠሰ መምጣቱን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚታዩት እንቅስቃሴዎች በማመልከት ላይ ሲሆኑ፣ የእነጄ/ል ተፈራ ማሞን እስር ተከትሎ በተለይም የአማራ ተዋላጅ የሆኑ የመከላከያ አባላት የተቃውሞ እንቅስቃሴ በማዘጋጀት ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሎአል። የአማራ ተወላጅ የሰራዊት አባላት ወያኔ በብሄራቸውና በኢትዮጵያ ልጆች ላይ እያደረሰ ያለው ጥቃት እንዲቆም ውሰጥ ለውስጥ እንቅስቃሴ መጀመራቸውን ያገኘነው መረጃ ያመላከተ ሲሆን፣ ወያኔም ይህን እንቅስቃሴ ለማፈን ባለ በሌለ ሀይል እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ለማወቅ ችለናል። ወያኔ ይቃወሙኛል የሚላቸውን የአማራና የኦሮሚያን ተወላጆች ካላጠፋ በስልጣን ላይ ለመቆየት እንደማይችል በማመኑ፣ በርካታ የብሄሮችን ተወላጆች በማሳደድ ላይ ሲሆን፣ የመጀመሪያውም በትር በእነ ጄ/ል ተፈራ ማሞ ላይ አርፎአል።

መላው የአገራችን የሰራዊት አባላት አገራችን ከድጡ ወደ ማጡ እየተጓዘች በመሆኑ ሊታደጋት እንደሚገባ ግንቦት 7 በተደጋጋሚ ጥሪ ሲያቀርብ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን፣ የሰራዊት አባላትም የግንቦት 7ትን ጥሪ በመቀበል ለተግባራዊነቱ በከፍተና ሁኔታ እየተንቀሳቀሱ እንደሚገኙ ኸመከላከያ የሚደርሰን መረጃ ያመለክታል።

## የህዝቦች በእጃቸው በያዙት መሳሪያዎች ሁሉ በመጠቀም ጭቆናን የማስወገድ መብት እንዳላቸው ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ለቢቢስ ተናገሩ

የወያኔው የይስሙላ ፍርድ ቤት መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ለማድረግ አሲረዋል ባላቸው ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ላይ የሰጠውን አስቂኝ የጥፋተኝነት ውሳኔ አስመልክቶ  የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነት እና የዴሞክራሲ ሊቀመንበር የሆኑት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ለእንግሊዝ የዜና ማሰራጫ ቢቢሲ በሰጡት ቃለምልልስ ህዝቦች በመርህ ደረጃ ጭቆናን ለማስወገድ ይጠቅመኛል ባሉት ነገር ሁሉ የመታገል መብት አላቸው ብለዋል።

ዶ/ር ብርሀኑ አያይዘውም ማንም በወያኔ አገዛዝ፣ በተለይም ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ፣ የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ መባል እንደማይቀርለት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ያውቃል ካሉ በሁዋላ፣ አሁን የይስሙላው ፍርድቤት ሰጠ የተባለው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከዚህ በፊትም በእርሳቸውና በጓደኞቻቸው ላይ የተሰጠ በመሆኑ አዲስ አይደለም ሲሉ ውሳኔው የሚጠበቅ እንደነበር ተናግረዋል።

ዶ/ር ብርሀኑ መፈንቅለ መንገስት መርተዋል ተብለው የሚቀርብባቸውን ክስ እንደማይቀበሉት በድጋሜ አረጋግጠው፣ ይሁን እንጅ ህዝቦች ጭቆናን ለማስወገድ ያመቸኛል የሚሉትን ዘዴ ሁሉ ቢጠቀሙ በመርህ ደረጃ ትክክል ናቸው ብለዋል።

ቢቢሲ በእስር ላይ የሚገኙት ጀግኖች የኢትዮጵያ ልጆች በወያኔ ምንደኛ ቡድን ድብደባ እንደተፈጸማቸው፣ በድብደባም ተገደው ቃል እንዲሰጡ እንደተደረጉና በአጠቃላይ ሰብአዊ መብቶቻቸው እንደተደፈረ የአለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች የሰጡትን መግለጫዎች ዋቢ በማድረግ ዘግቦአል።

ሰሞኑን የወያኔው የማፍያ ቡድን በእነ ጀ/ል ተፈራ ማሞ፣ በእነ ጀ/ል አሳምነው ጽጌና በሌሎችም እስረኞች ላይ የፈጸመው ድብደባ ኢትዮጵያውያንን በያሉበት ማስቆጣቱ ሲታወቅ፣ አሁን ደግሞ ጉዳዩ አለማቀፍ ትኩረትን እየሳበ መጥቷል። በጀግኖች የነጻነት ታጋዮች ላይ የሚደርሰው ግፍ ከእለት እለት ከመጨመር ውጭ ሊቀንስ እንዳልቻለ የሚደርሰን መረጃ የሚያመለክት ሲሆን፣ የወያኔው ተላላኪ ዳኛ አደም ኢብራሂም ድብደባ ለመፈጸሙ በቂ ማስረጃ የለም ሲል ጉዳዩን ማጣጣሉ ብዙዎችን አስገርሟል። ሰዎቹ መደብደባቸው በግልጽ እየታየ ህሊና የሚባል ነገር የሌለው ዳኛ ተብየው አደም ኢብራሂም የሰጠው መልስ ድሮውንም ችሎቱን የሚያስችሉት ሰዎች በወያኔ ተመርጠው የተቀመጡ ናቸው ብለው ሲከራከሩ የነበሩትን ወገኖች ትክክለኛነት አረጋግጧል።

የመሀል ዳኛው አደም ኢብራሂም የአፋር ተወላጅ ሲሆን፣ ከዚህ በፊት ለረጅም አመታት በጀርመን አገር የኖረና ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰ መሆኑን ግለሰቡን አስመልክቶ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል። አደም ኢብራሁም በአፋር ክልል ተቀጥሮ ሲሰራ ከቆየ በሁዋላ የወያኔ ካድሪዎች ማሰልጠኛ ወደ ሆነው ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ተልኮ ተምሮአል። ከዚያም በድሬዳዋ በስራ ላይ እያለ  ወያኔ ታማኝ ያላቸውን ሰዎች እየመረጠ ወደ አዲስ አበባ ሲያስገባ አደም ኢብራሂምም ታማኝ ናቸው ተብለው ከተመረጡት ሰዎች ውስጥ አንዱ ነበር። አደም ኢብራሂምን የሚያውቁ ሰዎች  እጅግ ክፉ ከሚባለው ከህወሀቱ አባል ልኡል ገብረማሪያም ቀጥሎ ሌላው ታዛዥና ጨካኝ ዳኛ መሆኑን መስክረዋል። ወያኔ የተወሰኑ ብሄር ተወላጆችን ለማጥቃት የአናሳ ብሄረሰብ ሰዎችን እንደሚጠቀም በቅንጅት አባላት ላይ የነበረው የፍርድ ሂደት የሚያመለክት ሲሆን፣ አሁንም በእነ ጀ/ል ተፈራ ላይ እየተፈጸመ ያለው ነገር ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው።

## አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የአገራችንን መሬት . . . ከገጽ 1 የዞረ

አንድ ስማቸው እንዳይነገር የፈለጉ ባለስልጣን ደግሞ እኛ አቅቶናል በውጭ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ድርጊቱን ተቃወሙልን ያሉ ሲሆን፣ ሌላው ተናጋሪ ግን ይህን ስርአት ተረባርበን ካልጣልነው  ከገባንበት የውርደት ማጥ ውስጥ መውጣት አንችልም ብለዋል።

የወያኔ አገዛዝ መሬት እንደልቡ የሚሸጠው  በዋነኝነት የኢጋጠመውን የውጭ ምንዛሬ ቀውስ ለመቅረፍ ቢሆንም፣ ከእነዚህ አገሮች ጋር መወዳጀቱ የስልጣን እድሜየን ያራዝምልኛል ብሎ እንደሚያምንም ለማወቅ ተችሎአል።

ግንቦት 7 ለወያኔ ብቻ ሳይሆን ከወያኔ ጋር ስምምነት የሚፈራረሙ ኩባንያዎችን ጭምር ማስጠንቀቁና በአሁኑ ጊዜ ህገወጥ ከሆነ አገዛዝ ጋር በመተባበር የአገሪቱን ሀብት ለመዝረፍ የሚደረገው ሙከራ በመጨረሻ ውጤቱ እንደማያምር መናገሩ ይታወሳል። የአገራችን ህዝቦች የመለስ ዜናዊን የሸፍታ አጋዛዝ ታግለው ካላስወገዱ  በስተቀር .አገራችን በቅርብ አመታት ውስጥ የውጭ አገራት መንግስታት እንደልባቸው የሚፈነጩባት ዜጎቻችን ደግሞ አሁን ካሉበት የሁለተኛ ዜግነት ደረጃም ወርደው ወደ ሶስተኛ የዜግነት ደረጃ የሚወርዱበት በአፓርታይድ ስርአት የምትመራ አገር እንደምትሆን ግንቦት 7 በተደጋጋሚ አስጠንቅቆአል፡፡

## የኦጋዴን ነጻ አውጭ ግምባር ወደ 1000 ሺ የሚጠጉ የወያኔ ወታደሮችን ገደልኩ ሲል ገለጸ

ግምባሩ በህዳር አንድ የፈጸመውን ጥቃት ማጠቃለሉን አስመልክቶ ባወጣው ዘገባ እስካሁን ድረስ ባለው መረጃ በተለያዩ ግምባሮች ከዘጠን መቶ ሰማንያ አምስት በላይ የሚሆኑ የወያኔ ወታደሮች መገደላቸውን ከዚህም ውስጥ አስራ ሁለት መኮንኖች እንደሚገኙበት፣ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች መቁሰላቸውንና 6 መኪኖች መውደማቸውንም ይፋ አድርጎአል። እንዲሁም ወታደራዊ መገልገያ ቁሳቁሶች፣ በእጅ የሚያዙ የጦር መሳሪዎች፣ ቦምቦች፣ የመገናኛ መሳሪዎችና ሌሎች ለስለላ ሲያገለግሉ የነበሩ እቃዎች ሁሉ መያዛቸውን ገልጾአል።

በሁሉም አቅጣጫ የመለስ ዜናዊ ጦር ክፉኛ ተሸንፎአል የሚለው የኦጋዴን ነጻ አውጭ ግምባር መግለጫ፣ በማያያዝም የወያኔ አገዛዝ የአጸፋ እርምጃ ለመውሰድ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ በተለይም ሲቪሎችን ለማጥቃት እንዳቀደ መረጃዎች እንደደረሱት   አስታውቋል። አገዛዙ በህዳር አንድ ጥቃት በተፈጸመባቸው ቦታዎች የሚገኙ ነዋሪዎችን በማንሳት ወደ ሌላ ቦታ ለማስፈር ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ኦብነግ ገልጾ፣ ከዚህ በተጨማሪም ለህዝባችን የመጣውን የእርዳታ እህል በፖለቲካ ምክንያት እንዳይከፋፈል ና ዜጎችንም አስነስቶ በካምፕ ውስጥ ለማጨቅ የሚደረገው የወያኔ ሴራ ወያኔን በጦር ወንጀለኝነት የሚያስጠይቀው ነው ብሎአል።

ወያኔ የደረሰበትን አስከፊ ጉዳት በመካድ ላይ ይገኛል የሚለው የኦጋዴን ነጻ አውጭ ግምባር መግለጫ፣ የአለማቀፍ ጋዜጠኞች ወደ ስፍራው እንዲገቡ ቢፈቀድላቸው እውነቱን ማረጋገጥ ይችላሉ፣ ወያኔ ግን እውነቱ እንዳይታወቅበት ጋዜጠኞች ወደ አካባቢው እንዲገቡ አይፈቅድም ብሎአል። ወያኔ በኦጋዴን የምፈራው ነገር የለኝም የሚል ከሆነ ነጻ የሆኑ የአለማቀፍ ጋዜጠኞች ወደ ስፍራው ተጉዘው ያዩትን እንዲዘግቡ ይፍቀድላቸው ሲል ለወያኔ ከባድ ጥያቄ አቅርቧል።

የወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ ከሶስት አመት በፊት የኦጋዴን አርበኞች ግምባርን በሁለት ሳምንት ውስጥ ጠራርገን ከክልሉ እናባርረዋለን ብሎ መናገሩ የሚታወስ ሲሆን፣ ከሶስት አመት በሁዋላ አሁንም ክልሉ ለውጭ አገር ጋዜጠኞች ክፍት ያልሆነ፣ የጸጥታም ስጋት ያለበት ክልል ከመሆን አልዘለለም።
የኦጋደን ነጻነት ግንባር ባለፈው ሳምንት በክልሉ የሚገኙትን 7 ከተሞች በውጊያ ከወያኔ ቁጥጥር ነጻ ማውጣቱን መግለጫ አውጥቶ እንደነበር   በርካታ አለም አቀፍ የሚዲያ ተቋሞች ሲዘግቡት እንደሰነበቱ የሚታወስ ነው።

## የኦባማ አስተዳደር በኢትዮጵያ ያለው የሰብአዊ መብት ጥሰትና የዲሞክራሲው መድረክ መጥበብ እንዳሳሰበው ገለጸ

የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ አገዛዝ የፖለቲካ መብቶችን ለማፈን የሚያደርገው ሩጫ፣ በየጊዜው የሚታዩት የሰብአዊ መብቶች መጣስ በእጅጉ እያሳሰበው እንደሚገኝ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ምክትል ሚኒስትር ካርል ዋይኮፍ መግለጻቸውን ብሉምበርግ ዘግቧል። ሚኒስትሩ  ለኢትዮጵያ ህዝብ ተብሎ የሚላከው እርዳታ ለፖለቲካ ድጋፍ ማስገኛ መዋሉን እንደሚያውቁ ገልጸው፣ ጉዳዩም የአሜሪካን መንግስት በእጅጉ አሳስቦታል ብለዋል። አሜሪካ በአገሪቱ ውስጥ በየጊዜው በሚታየው የፖለቲካ አፋና አለመደሰቱዋን የገለጹት ሚኒስትሩ ተቃዋሚዎች በየክልሎች ተዘዋውረው ከደጋፊዎቻቸው ጋር እንዳይገናኙ መደረጋቸውና ተደጋጋሚ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች መፈጸማቸው በእጅጉ እንዳስጨነቃቸው ተናግረዋል።

አሜሪካ ለወያኔ አገዛዝ ጠቀም ያለ የገንዘብ ድገፍ የምታደርግ አገር መሆኑዋ የሚታወቅ ሲሆን ባለፈው አመት ብቻ ለወያኔ ኔው አገዛዝ ዘጠን መቶ ሰላሳ ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ማድረጉዋን ብሉምበርግ ዘግቧል።

የአሜሪካና የእንግሊዝ መንግስታት ለኢትዮጵያ የሚላከው እርዳታ ለወያኔ የፖለቲካ ድጋፍ ማስገኛ እየዋለ ነው ሲሉ ቅሬታ ማቅረባቸውን  መዘገባችን የሚታወስ ነው።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org *ወይም* በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661